ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

<u>አዲስ አበባ</u>

ቀን: 24/02/2002
ቁጥር: ሀህዴሥ/ሰ/ዐ/17/03/200

**ጉዳዩ:-** <u>በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ ላይ በተደራደሩ ፓርቲዎች ገለፃ ላይ እንድንገኝ በመገናኛ ብዙሃን ስለተላለፈው ጥሪ ::</u>

ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎች ላይ መገኘትና ቦርዱም ለሚያደርጋቸው ጥሪዎች ምላሽ መስጠት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ እንደሚጠበቅ ይታወቃል:: ነገር ግን ከሰሞኑ በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተላለፈው የስብሰባ ጥሪ አግባብነት የሌለውና አጀንዳውም ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተናዋል:: ይኸውም፣

1. ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የመወያያ አጀንዳ ቀረፃና ሃላፊነት ወስዶ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ መጥራት እንጅ በሌሎች አካላት ለተወጠነ ዓላማ ማስፈፀሚያ መልዕክት አድራሽና አስተላላፊ መሆኑ አግባብ አይደለም::
2. የምርጫ ስነምግባር ደንብ የማውጣት ስልጣን በአዋጅ 532/2000 አንቀጽ 105 መሠረት የተሰጠው ለብሔራዊ የምርጫ ቦርድ መሆኑ እየታወቀና በዚህ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ለቦርዱ ሃሳብ ከማቅረብ ውጭ የማያልፍ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ የቦርዱ የማወያያ አጀንዳ ባልሆነው ሰነድ ላይ ተደራደሩ የተባሉት ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች "ገለፃ እንዲያደርጉላችሁ ተሰብሰቡ" የሚል ጥሪ ቦርዱ ማስተላለፉ ሕግን የተከተለ አይደለም::
3. በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ ላይ ተደራድረን ከሚሉት አራት ፓርቲዎች ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተሰጠው መግለጫ እንደተረዳነው፣ እነርሱ ለብቻቸው የተስማሙበት ሰነድ ለፓርላማ ቀርቦ የምርጫ ሕግ አካል እንደሚሆን ነው:: ነገር ግን በሀገራችን ባለው የሕግ ረቂቅ አቀራረብ አግባብ አንፃር ሲታይ ሁሉም የስነምግባር ደንቡ ተደራዳሪ ፓርቲዎች የፓርላማው አባል ስለመሆናቸው በፓርላማው ዕውቅና ያለማግኘታቸው እውነታ አካሔዱን ሕግን ያልተከተለ አድርጎታል::
4. ከላይ በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ በተጠቀሰው መግለጫ ውስጥ እንደተገለፀው "የምርጫ ስነምግባር ደንብ ላይ ተደራድረን" የሚሉት አራቱ ፓርቲዎች በሀገሪቱ በሕጋዊነት ተመዝግበው ከሚገኙትና ቁጥራቸው ከ90 በላይ ከሚሆን ፓርቲዎች ሁሉ የተለየ መብት እንደሚኖራቸው በደንቡ "የማስፈፀሚያ መመሪያ" ባሉት ሰነድ ላይ ማስፈራቸውን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ እያወቀ፣የብዙሃኑን የፖለቲካ ድርጅቶች የእኩልነት (የዕኩልነት) መብት ለመጋፋት ለሚንቀሳቀሱ ጥቂት ፓርቲዎች መድረክ የማዘጋጀቱ ተገቢነት በአዋጅ ከተሰጠው የገለልተኝነት መርህ ውጭ ነው:: በተለይም ይህ የጥቂት ፓርቲዎች ቡድን "የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት" የሚለውን አካል ለብቻው አቋቁሜአለሁ በሚልበትና ሌሎች ፓርቲዎች የዚህ ም/ቤት አባል መሆን ቢፈልጉ ደግሞ ፈቃጅና ከልካይ እኔ ነኝ እንደሚል እየታወቀ፤ ከዚያም አልፎ በሕጉ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የገንዘብ ድጎማን ይኸው ያቋቋሙት ም/ቤት በሚደርስበት ስምምነት እንደሚሆን የመደንገግ ዓላማ ሁሉ አንግቦ ለሚንቀሳቀስ አናሳ ቡድን ዓላማ ማራመጃ፣ የምርጫ

ቦርድ ሁኔታዎችን እያመቻቸ መሆኑ በሕግ ከተሰጠው ሃላፊነትና የገለልተኝነት መርህ የወጣ እርምጃ ነው።

ስለሆነም በሀገሪቱ ፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውንና ሌሎችንም ጨምሮ የስምንት ሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ፣ (መድረክ) በሀገራችን ኢትዮጵያ ሕግና የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሚታገል እንደመሆኑ፣ ለጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለፖለቲካ ፓርቲዎች ቦርዱ ያስተላለፈው የስብሰባ ጥሪ ከሕግ አግባብ ውጭ መሆኑ ታውቆ፣ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወሰድ አጥብቆ ይጠይቃል።

ሕግንና ሕጋዊነትን ማክበር ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ መሠረት ነው!

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ

ፊርማ

1. የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ /ኢሶዴፓ/ ----------
2. የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት /ደኢሕዴኅ/ ----------
3. ኦሮሞ ሕዝቦች ኮንግረስ /ኦሕኮ/ ----------
4. የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/ ----------
5. ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት /አረና/ ----------
6. የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት /ሶዴኃቅ/ ----------
7. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ /ኢዴአን/ ----------
8. አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ /አንድነት/ ----------